# ታምሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ

የኢትዮጵያ 4ኛው ምርጫ የሚከናወንበት ብዙም አልቀረውም። በምርጫው አሸናፊዎች ለመሆን ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ድርሻቸውን ይብዛም ይነስም ጥሩም ይሁን መጥፎ አቅጣጫዎች በመከተል የቻሉትን በመዘጋጀት መመረጥ ይገባናል እያሉ እንደቆዩም እንዳሉም በተግባር እያየነው ቆይተናል። ድርጅቶቹ ቢመረጡ ምን መስራት እንደሚችሉና አቅጣጫቸው ኢትዮጵያን የት እንደሚያደርሳት ከሞላ ጎደል ለሚመርጣቸው ህዝብ ለማስተዋወቅ ዓቅማቸውን የፈቀደው ሲደክሙ ቆይተዋል።

በብዙ መስፈርቶች ተመራጭዎችን መመዘን የሚያስችል ግንዛቤ ለማግኘት እንድንችል ዘንድ የተለያዩ አጋጣሚዎች ስንከታተል ቆይተናል። የየበኩላችን ግምት እንደወሰድንም እርግጠኛ ነኝ። ከዚህ በመነሳት እኔም በተወዳዳሪዎች የበኩሌን ያገኘሁትን ግንዛቤ ለመግለፅ ያህል ነው እንድፅፍ ያስገደደኝ።

ሁላችን ስለ ምርጫው የመሰለንን ነገር በነፃ የመግለፅ መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ያለብን ይመስለኛል። ኢትዮጵያ የመጠበቅ ሓላፊነት ለግለሰቦች ወይም ለመንግስት የተሰጠ ሓላፊነት ብቻ አይመስለኝም። ኢትዮጵያን የመጠበቅ ሓላፊነት ለማንኛው ኢትዮጵያዊ የሚመለከት ነገር ነው። ሓላፊነታችን ባንወጣ በታሪክ መወቀሳችን የግድ ይሆናል። ስለዚህ ከግለሰብ እስከ በተደራጀ መልኩ መስራት የሚገባን መስራት ይኖርብናል። የትም ብንኖር ኢትዮጵያ የመጠበቅ ግዴታ አለብን። ከዚህ በመነሳት ላለፉት ወራት የቻልኩትን ያህል ለማለት በተደጋጋሚ እየጻፍኩኝ ቆይቻለሁ። ግዴታየ ስለ ሆነ። ያንን ግዴታ ለመወጣት ደግሞ ሁላችን ከመንግስት ጋራ መስራት የለብንም። ስለዚህ ሁላችን ግዴታችና ሓላፊነታችን እንድንወጣ ኢትዮጵያዊነታችን ያስገድደናል።

የፊታችን ምርጫ አስመልክቶ በኢህአዴግና ተቃዋሚ ድርጅቶች በቀረቡት የመከራከርያ አጀንዳዎች አስመልክቸ የመሰለኝ ያህል ያገኘሁት ግንዛቤ ስፅፍ ቆይቻለሁ። ዛሬ ክርክሮቹን አስመልክቸ ብዙ የምለው ነገር አይኖረኝም። ትንሽ ነገር በማንሳት ግን ወደ የክርክሮች አጀንዳዎች ጎራ ማለቴ አይቀርም። የዛሬ ፅሑፌንም ምርጫውን አስመልክቶ የተፃፈ ስለሆነ።

በግብርና ፖሊሲ በነበረው ክርክር ኣቶ ልደቱ ኣያሌው ያሉትን ነገር በብዙ ድርጅቶችና ብዙ ግለሰዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች የኢህአዴግ ደካማነት ይገልፃል በማለት የሚያነሱት የሰማሁት ነገር ቢኖር ጠቅላይ ሚንስተር መለስ ለኢትዮጵያ ህዝብ በሚቀጥሉት ዓስር ዓመታት ምን ይመኛሉ? ተብሎ ሲጠየቁ “በቀን ሶሥት ግዜ እንዲበላ” ብሎ ነበር። እንኳን በ10 ዓመታት እስከ አሁን በ18 ዓመታት ውስጥ ግን ያ ምኞት እውን አልሆነም። በማለት ሲወቅሱ ሲጠይቁና ተደምጠዋል።

ተቃዋሚ ድርጅቶች ምን ብሎ ስለ ጉዳዩ እንደ ተናገሩ መድገሙን ግዜ ማጥፋት ይሆናል። የበኩሌን ሓሳብ ግን ሳላስቀምጥ ማለፍ ኣልወድም። ጠቅላይ ሚኒስተር ያ ምኞት ነበራቸው። በግልፅም የተናገሩት ነገር ነበር። ለምን ያ ነገር ተመኙ? ለምንስ ነበር ከ10 ዓመታት በታች ያልገመቱት? እንዴትስ 100 % ምኞታቸውን ኣልተሳካም? የሚለውን ጥያቄ ተገቢ መልስ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ይመስለኛል።

ኣንድ መሪ ምኞት ኣስቀመጠ ማለት በትክክል የሚሆነውን ኣስቀመጠ ማለት ኣይደለም። ምኞት ማለት ሊሳካም ላይሳካም ይችላል ማለት ይመስለኛል። በጣም እርግጠኛ ነኝ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት 3 ግዜ በቀን ይመገባል ኣላሉም። ተመኙለት እንጂ። ኣቶ ልደቱ ኣያሌውና ሌሎች በፓርቲ ሲደራጁ በተለይ በፓርቲ መሪነት ባሉበት ግዜ ጠቅላይ ሚኒስተር ለመሆን ፓርቲያቸው መንግስት እንዲሆን ያልተመኙበት ቀን የነበረ ኣይመስለኝም። ባለፈው ምርጫም ኣሁንም እናሸንፋለን ብለው በእርግጠኝነት ተናግረዋል። ከምኞት ኣለፍ ብለዋል። ባለፈው ምርጫ በእጃቸው ያለውን ነገር ማድረግ የሚችሉት ነገር ግን መፈፀም ኣቃታቸው። ኢህኣዴግን ለማሸነፍ ከኢህኣዴግ መብለጥ የሚችሉበት ነገር መፍጠር ይችላሉ። በ18 ዓመታት ግዜ ግን የፈጠሩት ድርጅት በምንም መልኩ ተስፋ የሚሰጥ ሆኖ ኣልታየም። በ18 ዓመታት ግን ጥንካሬ ሃገርን ለመምራት የሚያስችል ብቃት መገንባት ይቻል ነበር። ኢህኣዴግ ከባዱን የ17 ዓመታት የትጥቅ ትግሉ እንኳን 18 ዓመታት ኣልፈጀበትም። በዛን 17 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎኑ በማሰለፍ ነበር ደርግን ያሸነፈው። ህዝብ ሓይል ነው። ህዝብን ለትጥቅ ትግል ማሰለፍ ካልተቻለ ደርግን ማስሸነፍ ኣይቻልም ነበር። በዛ ክፉ የሞት የዕልቂት ግዜ ግን ኢህኣዴግ የህዝብ ድጋፍ ማግኘት የቻለበትና በትጥቅ ትግሉ ማሰለፍ የቻለበት ቆንጆ ስራ ሰርተዋል። ተቃዋሚዎች ግን ሰላምዊ ሁኔታ ባለበት ውጥረትና ስጋቶች በሌለበት የፈለግከውን በፈለግከውን መንገድ ተደራጅተህ መንግስትን መቃወም በሚቻልበት ግዜ ህዝብን በጎናቸው የማሰለፍ ምንም ዓይነት ስራ መስራት ኣቃታቸዋል። ይህንን ማድረግ የሚችሉት ሳያደርጉ በመቅረታቸው ምኞታቸው ኣልተሳካም ኣልሆነላቸውም። ማድረግ የሚገባቸውን ትተው ኣስፈላጊ ባልሆነ ጉዳይ ግዜ ማባከን ላይ ይገኛሉ። የሚገርመው ነገር እኛ ምን ሰራን በ18 ዓመታት ውስጥ ብሎ መጠየቅ ሲገባቸው ኢህኣዴግ በ18 ዓማታት ላደረገውን ነገር ይተቻሉ። እንዲህ ስያጋጥማቸው የትግራይ ሰዎች የሚሉት ነገር ኣለ። "ኣድጊ ያ ዘይብሉስ በቕሊ ይንዕቕ" ትርጉሙ "ኣህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል" ማለት ነው።

ለምን ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ በ10 ዓመታት ውስጥ ይህንን ተመኙ? ሁላችን በመሰለን መንገድ ልንመልስ እንችላለን። ስለሆነም የበኩሌን ሓሳብ ልግለፅ። ኢትዮጵያ በዛን ግዜ የነበራት የደህነት ደርጃ ግምት ውስጥ በማስገባት በ10 ዓመታት ውስጥ ሁሉም ሕብረተሰብ የበኩሉን ቢሰራ። ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ከነ ልዩነታቸው ግን ደግሞ ለኢትዮጵያ ዕድገት ኣንድ ሓይል ኣንድ ክንድ ሆነው ይሰሩ ይሆናል የሚል ፅኑዕ እምነት ስለነበራቸው። ኢትዮጵያ በዛን የምኞት 10 ዓማታት ጦርነት ባይገጥማትም በማለት ይመስለኛል ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ያ የተመኙት። ግን እንደተመኙት ኣልሆነላቸውም። ለምን?

በሕብረተሰቡ በኩል ብንመለከት በመንግስት መራቤት የሚሰሩ ብዛት ያላቸው ሰዎች በሙስና የተበከሉ በየ የስራ ዘርፉ ይገኛሉ። ሕብረተሰቡ ይህንን በሽታ ለማጥፋት የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ አልቻለም። እንዲያውም በሽታው በይበልጥ እንዲስፋፋ በር እየከፈተ ስያስተናግዳቸው ይታያል። ሙስና ደግሞ በጣም ከባድ በሽታ አገርን ወደኋላ የመጎተት ዓቅም ያለው ነው። ይህንን በሽታ በመንግስት ሓይል ብቻ ማጥፋት ከቶ የማይቻል ነገር ነው። ይህንን በሽታ የሚጠፋው በህዝብ ጠንካራ ተሳትፎና ህዝብና መንግስት ለዚህ በሽታ ለማጥፋት አንድ ላይ በመሆን መስራት ቢይችሉ ነው። ኢህኣዴግ ሙስናን ለማጥፋት ነገሮችን እየዘየደ እየፈጠረ በሔደበት ቁጥር በህዝቡ በኩል ግን ውጤታማ ስራ አልተሰራም ገና። ብዙ ሰዎች ጉዳያቸው ከሚገባቸው ነገር በላይ እንዲፈፀምላቸው ሌላውን ወገን ጎድቶ ለመጠቀም ለመንግስት ሰራተኞች በሙስና እንዲበከሉ እያደረጉ ይገኛሉ። በደሃው አገርና መንግስት የሚኖር የመንግስት ሰራተኛ ኣይቶት የማያውቀውን ገንዘብ እንደሚሰጠው ሲነገረው ባለው የኑሮ ጉስቁልና ምክንያት ሳይወድ ትክክል ነገር ከመስራት መንግስት የሰጠውን ሓላፊነት ከመወጣት ወዲ ሙስናው ጎራ ይላል። በ10 ዓመታት ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ የተመኙት እንዳይሳካ የሕብረተሰቡ ኣስተዋፅኦም ቀላል ኣይደለም።

ሌላው የጠቅላይ ሚኒስተር መለስ የ10 ዓመታት ምኞት እንዳይሳካ ምክንያት የሆነው ተቃዋሚ ድርጅቶች በማንኛው የመንግስት እንቅስቃሴ ዕንቅፋት ሆነው በመገኘታቸው ነው። ሁላችን የምናውቃቸው ምሳሌዎች ማስቀመጥ ይቻላል።

1) ስለ ሓይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦች ግንባታ ኢህኣዴግ ሊሰራ በሚነሳበት ግዜ ለዓለም ባንክ መንግስት ብድር በሚጠይቅበት ወቅት ተቃዋሚ ድርጅቶች ብድር እንዳይሰጥ ያ ገንዘብ ኢህኣዴግ በሌላ ጉዳዩ ልያውለው ነው እያሉ ግድቦቹን እንዳይሰሩ ለማድረግ የበኩላቸው ኣድርገዋል።

2) መንግስት የሚሰጠውን ዕርዳታ በትክክል ለሚመለከተው ህዝብ ስለማይደርስ መሰጠት የለበትም በማለት ለዕርዳታ ሰጭዎች በተደጋጋሚ ኣስታውቀዋል።

3) ተማሪዎች በሰላም ተምረው ኢትዮጵያ ከደህነት ለመውጣት የበኩላቸው እንዳያደርጉ ባልሆኑ ምክንያቶች ኣነሳስቶ ለረብሻ ዳርገዋል።

4) በብሔርና ብሔረሰቦች በመፈቃቀር የተመሰረተ ኣንድነት እንዳይኖር እኩልነት የለም። ትግራይ ከሌላው ኢትዮጵያ በይበልጥ ተጠቃሚ ሆናለች። በስልጣን ያሉ ሰዎች የዛን ብሔር ናቸው። ወዘተ እያሉ በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ቅራኔ እንዲኖር የበኩላቸው እያደረጉ መጥተዋል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ በቀን ሶሥት ግዜ እንዳይበላ ተቃዋሚ ድርጅቶች የበኩላቸው ትልቅ ሚና ተጫውተዋል ኣሁንም ቸዋታው ውስጥ ነው ያሉት ሶሥት ግዜ በቀን የመብላት ነገር እንዳይረጋገጥ የቻሉትን በማድረግ ይገኛሉ።

ሌላው በኢትዮ-ኤርትራ የተነሳው ጦርነት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ወደኋላ እንዲጎተት የራሱን ከባድ አስተዋፅኦ አድርገዋል። እስከ አሁንም በአሸባሪነት እየተሰሩ ያሉትን የበኩላቸው ዕንቅፋት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ እየጣሉ ይገኛሉ። ጠቅላይ ሚኒስተሩ ምኞታቸው ሲገልፁ ግዜ በመንግስት መስራቤቶች የሚሰሩ ሰዎች በፖለቲካ የሚደራጁ ሓይሎችና መንግስት ሁሉም በአንድነት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አንድ ላይ በመሆን ይሰራሉ የሚል ግምት ስለ ነበራቸው ይመስለኛል በ10 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ሶሥት ግዜ በቀን እንዲበላ የተመኙት። ሆኖም ግን ያ ያመኑት የበጋራ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት መስራት እንዳሰቡት ሳይደረግ ስለቀረ ነው ሶሥት ግዜ በቀን ለመብላት ያልተቻለው።

ተቃዋሚ ድርጅቶች ለምን ጠቅላይ ሚኒስተር የተመኙት ሳይሆን ቀረ? ያንን ለማሳካትስ ድርሻችን ምን ነበረ? ድርሻችን ለምን አልተወጣንም? በዚህ ጉዳይ እኛስ ከመጠየቅ እንቀራለን ወይ ብሎ ራሳቸው መጠየቅ ይገባቸው ነበር። በትክክል በቀን ሶሥት ግዜ አለመመገብ ብያሳስባቸው።

ተቃዋሚ ድርጅቶች ማንኛውም የኢህአዴግ እንቅስቃሴ እንደተቃወሙት ነው። መንግስት ይህንን አልሰራም። ይህንን አላደረገም። ከማለት ውጭ ቁምነገር ሲሰሩ አልታዩም። ኢትዮጵያ የሁሉም ናት። ለኢትዮጵያ ዕድገት ከግለ ሰብ እስከ ድርጅት የበኩላቸውን መወጣት ይገባቸው ነበር። እየታየ ያለውን ግን በተቃራኒው ነው። መንግስት ወደ ማንኛው በተራመደበት አቅጣጫ ዕንቅፋት መሆን ብቻ። ታድያ መንግስት ዘመቻው ድህነትን ለማጥፋት ብቻ አይደለም ግዜውን ሙሉ በሙሉ የሚያሳልፈው። ያ ዕንቃፋት ለመጥረግም ሌላ ተጨማሪ ግዜና ስራ ያስፈልጋል። ዕንቅፋቱ ባይኖር ኖሮ እንዲያውም ጠቅላይ ሚኒስተሩ ከተመኙት በላይ ኢትዮጵያ ታድግ ነበር። እንደ ግምቴ ብያንስ ብያንስ አሁን ከደረሰችበት በይበልጥ ታድግ ነበር። ግን ምን ይደረግ አለመታደል ነው።

ተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጣቸውን የመፈተሽና የጎደላቸውን ማየት ቢቻላቸው ኖሮ ጠቅላይ ሚኒስተሩ ያሉት ለምን አልተሳካም ብሎ መጠየቃቸውን መልሶ ያሳፍራቸው ነበር። ያንን ለማድረግ ግን ተፈጥሮ የላቸውምና ለሰሩት ጥፋት በሌላ ማሳበብ ተፈጥሮአቸው ያስገድዳቸዋል።

ባለፉት የመከራከርያ ነጥቦች የሚመለከት አስተያየት በዚሁ ልቋጨውና ወደ ዋናው ለመፃፍ የተነሳሁበት ልግባ።

ምርጫ በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ይካሔዳል። ይህንን በፊታችን የሚጠበቀው ምርጫ ሰላማዊና የተረጋጋ እንዲሆን የሚመኙ እንደሚኖሩ በተቃራኒ በሰላም እንዳይሳካ ብጥብጥና ረብሻ እንዲኖሮውና የተሳካ እንዳይሆን የሚፈልጉም አሉ። እነዚህ ያልተሳካ ምርጫ እንዲሆን የሚመኙት በመደራጀት በውስጥም በውጭም የቻሉትን ያህል ያላቸውን ዓቅም በመጠቀም ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል። በምርጫው ግዜም ይህ የረብሻና ብጥብጥ ስራቸው በይበልጥ ለማከናወን ወደኋላ አይሉም።

እነዚህ ምርጫውን ሰላማዊ እንዳይሆን የሚለፉት እነማን ናቸው? ለምንስ ነው እንዲህ የሚፈልጉት? በዚ ረብሻ ተጠቃሚና ተጎጂ ማን ይሆናል? ብሎ ማየቱ

በጣም አስፈላጊና ተገቢ ይመስለኛል። ከዚህ በፊት ግን ኢህኣዴግ ደሞክራሲያዊ መንግስት ነው ወይ? ኢህኣዴግ ቢመረጥ ለኢትዮጵያ ይጠቅማል ወይም ይጎዳል? ለምን? ብለን በመጠየቅ መመለስ ያስፈልገናል። ስለዚህ የበኩሌን ኣመለካከት ለመስጠት ልሞኩር።

ኢህኣዴግ በትጥቅ ትግል ዘመኑ ስለ ኣሁንዋ ኢትዮጵያ የነበረውን ዓላማ እኔም ታጋይ በነበርኩበት ዘመን ያወቅኩት ነገር ቢኖር ደርግ ከወደቀ በኋላ የሽግግሩን መንግስት በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች የተመሰረተ መሆን እንዳለበት። ከዛ ቀጥሎ የሚኖረው መንግስት በህዝብ የተመረጠ መንግስት መሆን እንዳለበት። ኢህኣዴግ በምርጫው ቢሸነፍ ለኣሸናፊው መንግስትነት ማስረከብ እንዳለበት። የህዝብ ወሳኝነት በተግባር ማሳየት እንደሚኖርበት። የታገለበት ዋናው ዓላማም ህዝብ የስልጣን ባለ ቤት ለማድረግ እንደመሆኑም መጠን ህዝብ የመረጠው መንግስት መሆን እንዳለበት ገና በረሃ በነበርንበት የታመነበትና ለተግባራዊነቱን መስዋእት የተከፈለበት ጉዳይ ነው። ይህም ባለፉት 18 ዓመታት ታይተዋል በዚህ 19ኛው ዓመትም የሚደገም ይሆናል። ይህንን የኢህኣዴግ ዕውነተኛ ዓላማና ባህሪ ነው። ይህንን ባህሪ በምንም መንገድ የማይቀየር የማይሻር የኢህኣዴግ ዕውነተኛ መመዘኛ ነው። በማንኛው ግዜና ቦታ ነባሪና ተፈፃሚ እየሆነ መጥተዋል ወደፊትም ይቀጥላል። ህወሓት ኢህዴን ኦህዴድ እየፈፀሙት የመጡትና ለዚህ ዓላማ ማሳካት የቆሙ ድርጅቶች ነበሩ በበረሃው የትጥቅ ትግል ዘመናቸው። ኢህ ኣዴግ መንግስት ከሆነም በኋላ ያ የበረሃ እምነትና ዓላማ በይበልጥ ተግባራዊ እያደረገው መጥተዋል። ታሪክ የመሰከረውም ይህንኑ ነው።

ዴሞክራሲ ምን ማለት ነው? ብዙ ሰዎች ወይም ድርጅቶች በስሕተት እየተረጎሙት የመጡ ይመስለኛል። እንደነሱ ዴሞክራሲን ኣተረጓጎም በስልጣን ላይ ኣንድ የፖለቲካ ድርጅት ወይ መሪ ብዙ ኣለመቆየት። ለሌላው ስልጣን ላልቀመሰ ቦታውን መልቀቅ ኣድርገው ነው የሚገልፁት። ይህ ባይሆን ግን የሚኖረው መንግስት ዴሞክራሲያዊ ሳይሆን ኣምባገነን ነው ይሉታል። በዚህ መልኩ የሚተነትኑት ወገኖች ደግሞ ዴሞክራሲያውያን ነን በማለት ዴሞክራሲያውያን ለመምሰል ይሞኩራሉ። ዋናው የዴሞክራሲ ትርጉም ግን ብዙሃን ያመኑትና የወሰኑት መቀበል ነው። በስራ ላይ ማዋል ማለት ነው። በሌላ ኣነጋገር ጥቂቶች የግድ በብዙሃኑ ስር ሆኖ እነሱ (ጥቂቶቹ) ያላመኑት ግን ብዙሃኑ የፈለጉት መፈፀም ማለት ነው። ስለዚህ ኣንድ መንግስት ወይም መሪ በምርጫ ብዙ ግዜ ብያሸንፍና ለ30ና 40 ዓመታት ወይም ከዛ በላይ በስልጣን መቆየቱ እንዴት ነው ዴሞክራሲያዊነት ኣይደለም ኣምባገነንነት ነው የሚባለው። ህዝብ የመረጠው መንግስት ወይም መሪ የፈለገውን ያህል ግዜ በተመረጠበት ስራ መቀጠሉ በትክክል ዴሞክራሲያዊነት ነው።

ኣምባገነን ሰዎች ወይም ሓይሎች ግን ህዝብ ሳይመርጣቸው ስልጣን ላይ መምጣት የሚፈልጉ ናቸው። ምርጫው ተጭበረበረ እንዲህ ሆነ እያሉ ሰበብ በመፍጠር ያልሆነውን ያልተፈጠርውን ነገር እያመጡ ሌሎችን ማስወንጀል የሚያዘወትሩ ሓይሎች በሙሉ ከመስራት ይልቅ ኣምባገነን ኣመለካከት እያራመዱ ግዝያቸውን ይፈጃሉ። ሳይመረጡ ህዝብን በማደናገር በግርግር ስልጣን ይመኛሉ። ኣምባገነኖች በህዝባቸው እምነት የሚባል ነገር ከቶም የላቸውም። ምኞታቸው ለማሳካት

ከህዝባቸው ጋር አይጠጉም። ይርቃሉ። ህዝብ ጋር ቢቀርቡ ባዶ ሆነው ማሳየት የሚችሉት ነገር እንደሌላቸው በሚገባ ያውቃሉ። ለህዝብ መጥቀም አለመቻላቸው ህዝቡ አይቶ እንደማይቀበላቸው እርግጠኞች ሆነው ያውቃሉ። ስለዚህ እዛም እዛም እየሔዱ ከባዳ ጋራ ይለማመጣሉ። ስልጣን ለመያዝ ያግዙን ይሆናሉ ከሚለውን ፍላጎት።

የኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊነት በምንም መንገድ በጥያቄ ውስጥ መግባት የማይገባውና የሌለበት ጉዳይ ነው። እኔ በዓለማችን የትኛው መንግስት ነው ዴሞክራሲያዊ ተብየ ብጠየቅ ኢህአዴግ ነው ብየ እመልሳለሁኝ። ይህንን ያልኩት የማይዋጥላቸው እንዳሉ አውቃለሁኝ። ሓቁ ግን ይህንን ነው።

በኢትዮጵያ ታዳጊ ዴሞክራሲ ጀማሪ ዴሞክራሲ ነው የሚባለው ነገር አለ። ይህ ማለት በኢህአዴግ ያለው ዴሞክራሲ ነው ማለት አይደለም። በተጠቃሚው ህዝብ ገና አልተለመደም። አጠቃቀሙ በሚገባ ገና አልለመደውም ማለት ነው እንጂ በኢህአዴግ ያለው ዴሞክራሲ በዓለማችን አሉ ከሚባሉ ዴሞክራሲያውያን መንግስትታት ትልቁ ስፍራ ያለው በኢህአዴግ እየተሰራበት ያለውን ዴሞክራሲ ነው። በተጠቃሚው ዘንድ ግን ያልተለመደና ገና እንዲለመድ ግዜ የሚያስፈልገው ነገር መሆኑን የታወቀ ነው። በ18 ዓመታት መለወጥ የነበረበት አይደለም። በዴሞክራሲ ያለው የሕብረተሰቡ አመለካከት እንዲለወጥ ዘንድ ታላቅ ቦታ ካላቸው ነገሮች አንዱ በሕብረተሰቡ በሳላ የፖለቲካ ስራ ማከናወን ነው። በቂ ግዜ ደግሞ ያስፈልገዋል። ተጠቃሚው ህዝብ ዴሞክራሲ ገና አልለመደውም ገና አጠቃቀሙ ላይ ብዙ ችግሮች አሉ ለማለት ያስቻለኝን በሚቀጥሉት ሁለት ምሳሌዎች ልጥቀስ።

አንድ ግዜ ከጓዶኞቼ እየተጫወትን እያለን አንዱ ያለውን ላካፍላቹህ። ሰውየው የትግራይ ሰው ነው። ሚስቱ ደግሞ አማራ ነች። ባለፈው የ97ቱ ምርጫ ግዜ ሚስትየው ወደ ቤተሰቦችዋ አገር ቤት ደውላ “ማንን ልትመርጡ ነው”? ብላ ስትጠይቃቸው “ምን እናደርጋለን ባልሽን እንዳይከፋው ኢህአዴግን እንመርጣለን” አሉዋት ብሎ አጫወተን። ይህ የሚያሳየን አንድ ሰው ሲመርጥ የተሰጠውን መብት ተጠቅሞ ወይም መጠቐም እንዳለበት በመተማመን ሳይሆን እንትና እንዳይከፋው ብሎ እንጂ በትክክል ያመነበት ያንን ብመርጥ ይጠቅመኛል። ያንን ብመርጥ ይጎዳኛል በማለት አይደለም። ይህ የሚያሳየ ደግሞ የራስህን መብት በራስህ መሻር ነው መሆኑ ነው። በኢትዮጵያ ያለው ዴሞክራሲ ጀማሪ ወይም ያላደገ ነው ለማለት የሚያበቃን እንደ እነዚህ ዓይነቶቹ ነገሮች ስናይ ነው።

ሌላው አንድ አንድ ሰዎች አንድ መንግስት ወይም መሪ ብዙ መቆየት የለበትም። አንድ ነገር ለብዙ ግዜ ማየት ይሰለቻል ሌላ አዲስ ፊት ማየት መልካም ነው። የሚሉት ፍልስፍናም አለ። በስልጣን ላይ ይምጣና እንየው የሚሉ የዛን ወደ ስልጣን የሚመጣው ድርጅት ወይ ግለ ሰብ ማንነት ወይም ዓላማ ሳይሆን የሚያዩት መለወጡን ብቻ ነው የሚፈልጉት። ይህ ዓይነቱ አባባል እዚህ ባለንበት አገርም አውስትራልያም የሚሰማ አባባል ነው። የዴሞክራሲ ተጠቃሚው በሚገባ አለመጠቀም የተጠቃሚው ጉድለት ነው። እና በኢትዮጵያ ያለው ገና ያላደገ ዴሞክራሲ ነው ማለት ተጠቃሚው ራሱን እየገደበው እንጂ ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ

ካለመሆኑ የመጣ ኣይደለም። በኢህኣዴግ ያለው ዴሞክራሲ ጀማሪ ነው ማለትም ኣይደለም።

በኢትዮጵያ ውስጥ በኣሁኑ ሰዓት ሌላ ድርጅት ቢመረጥ ኢትዮጵያን በክፉኛ ይጎዳታል። የኢህኣዴግን መምረጥ ለወደፊት የኢትዮጵያ ዕድገት በጣም ወሳኝ ነው። በዚህ ምርጫ ኢህኣዴግን በልጠ መመረጥ የሚችል ድርጅት በበኩሌ ኣላገኘሁም። ተቃዋሚ ድርጅቶች ስለ ዓላማቸው ስለ ዴሞክራስያዊነታቸው ለማስተዋወቅ ደፋ ቀና ሲሉ ሰብተዋል። ቀና ደፋ ያሉበት ጉዳዮች ስንመለከት ግን ኢትዮጵያን ኣለመጥቀሙን በብዙ መንገድ መተንተን ይቻላል። በተግባርም የምናየው ነገር ቢኖር ተቃዋሚዎቹ ዴሞክራሲያውያን ኣለመሆናቸው ነው። ተቃዋሚዎቹን በሌላ መመዘኛ መንገድ ብንመለከታቸውም ከኢህኣዴግ ሌላ ድርጅት ላለመመረጥ ምክንያት እናገኛለን። ዓቅማቸው ብንመለከት ገና ያልበሰሉ እንኳን ኢትዮጵያን ሊመሩ በድርጅት መልክ ጠንካራ ናቸው ለማለት የሚያስፈራ ስጋት ላይ የሚጥል ሁኔታ ላይ ነው የሚገኙት።

ኢዴፓ ብንወስድ ለምርጫው በሚካሄደው ክርክሮች በተደጋጋሚ ኢዴፓን በመወከል የቀረበው ኣቶ ልደቱ ኣያሌው ነበር። ለምን በተደጋጋሚ ኣቶ ልደቱ ብቻ? ክርክሩ በእኔ ግምት ሁለት ተልእኮዋች ይኖረዋል። ኣንደኛው ስለ ድርጅታቸው ዓላማ ማስተዋወቅ። ሁለተኛው ደግሞ የድርጅቱን ሰዎች ማስተዋወቅ ይሆናል። ኣቶ ልደቱ ኣያሌው ግን ኣብዛኛው ክርክር ይዘውት ነበር። ይህንን ደግሞ ከዓቅም ማነስ ይመስለኛል። ኢዴፓ ካለ ኣቶ ልደቱ በስተቀር ሌላ ሰው የለውም ለማለት የሚያስችል ይመስለኛል። ሌላው ኣቶ ልደቱ ያሉት ነገር በግብርና ፖሊሲ ክርክር ላይ ኢህኣዴግ እንዳለፉት ክርክሮች እኛን በሚያመጣው ነገር ግዝያችን እንድናሳልፍና ፕሮግራማችን ሳናስተዋውቅ ግዜ እንድናባክን የምታደርጉት ነገር ደርሰንበታል። ከኣሁን በኋላ በእናንተ ዘዴ ኣንታለልም። ዓይነት ነገር ተናግረዋል። ይህም ከዓቅም ማነስ የሚመጣ ኣነጋገር ነው። ተቃራኒህ መብለጥ ያለብህ ቀድመህ ነው እንጂ ይህማ ጅብ ከሔደ ውሻ ጮሐ ይመስለኛል። በወሳኝ ብዙ ኣጀንዳዎች ግዜ ካባከኑ ምርጫ ብያሸንፉም በኢትዮጵያ ጉዳይ ዘግይቶ እንደሚገባቸው እየነገሩን ይመስለኛል። በክርክሩ እንዳንቀላፉት በስልጣን ላይም ልያንቀላፉ ነው ማለት ይመስለኛል። ከተናገሩት ሌላ የተገነዘብኩት ነገርም ኣለ። ከዛን ክርክር በፊት የነበሩ ኣጀንዳዎች ምን ማለት እንዳለባቸው በትክክል ኣውቆ የገቡበት ኣልነበረም ማለት ነው። በዚህ ምክንያት እንጂ ኢህኣዴግ በኣበጀው ወጥመድ ስለገቡ ኣልነበረም ብዙ ነገር ኣንስተው ህዝቡን ለማሳየት ያልሞከሩት። ከግብርና መከራከርያ በኋላ የቀጠለው ክርክርና በግብርና የተካሔደው ክርክር በተሟላ ኣልተከታተልኩትም። በግብርና ፖሊሲ ቅንጅትም በዛ ያለ ሓሳብ ለመግለፅ የሞኮረ ይመስለኛል። ግን ሁሉም ኣጥጋቢ ትንተናዎች ኣላቀረቡም። ዓቅም የማነስ ጉዳይ ነው። በዚህ ዓቅም ኢትዮጵያን መምራት እንደማይችሉ በግልፅ እያሳዩን ነው።

ስለ ዴሞክራሲ ሲነሳም መድረክ መውሰድ ይቻላል። በመድረክ ውስጥ ኣቶ ስየ ኣብርሃ ኣቶ ገብሩ ኣስራት ወ/ሮ ኣረጋሽ ኣዳነና ሌሎች የኢህኣዴግ ባለስልጣናት ይገኙበታል። ስለ ዴሞክራሲ ሲሰብኩ ታይተዋል። ከላይ እንደገለፅኩት የዴሞክራሲ ዋነኛና ብቸኛ ትርጉሙ ጥቂቶች በብዙሃን ስር ማለት ነው። የድሮው የኢህኣዴግ የኣማራር ኣባላት የኣሁኑ የመድረክ ኣመራሮች በህወሓት በነበሩበት ወቅት በዛን

ግዜ በህወሓት በተፈጠረው ችግር እነዚህ የአሁኑ መድረክ የዛን ግዜ ህወሓት በድምፅ በተሸነፉበት ወቅት በብዙሃኑ አንገዛም ብሎ ያመፁና ለዴሞክራሲ ተገዢ ያልሆኑ እንዴት ለምርጫ እንደቀረቡ አይገባኝም። በዴሞክራሲ እየዘመሩ ይገኛሉ በተግባር ግን ወድቀዋል። ሌላው የቅርብ ግዜ በአንደበታቸው የገለፁልን ዴሞክራሲያውያን አለመሆናቸውን የሚመለከት ቢኖር ኣቶ ስየ ኣብርሃ እኔ በተንቤን ገብሩ ኣስራት በመቀሌ ካልተመረጥን ምርጫው ተጭበርብረዋል ማለት ነው። ያሉትም ያ ብሸነፍም አልገዛም የሚል ወናቸው ጥንካሬ ሲሰጣቸው ነበር በህዝብ ፊት ደረታቸው ነፍቶ የተናገሩት።

ስለ ተቃዋሚ ድርጅቶች በከፊል ለመጥቀስ የመከርኩትና ከዚህ በፊት ስፅፋቸው በነበርኩት ጉዳዮች ስመለከትና ስመረምር ተቃዋሚ ድርጅቶች በትክክል መመረጥ ኣይገባቸውም። ቢመረጡ ጉዳት ነው። ቢመረጡ ኢትዮጵያ አሁን የደረሰችበት ደረጃ በመጠበቅ ዕድገትዋን ለማፋጠን ወደፊት መራመዱን ትታ ወደኋላ በቀጥታ ተመልሳ አደጋ ላይ ትወድቃለች። ወደኋላ ለመመለስ ደግሞ 18 ዓመታት መጠበቅ ኣያስፈልጋትም። በጣም ኣጭር ግዜ እንጂ።

በሚደረጉ ክርክሮች ተቃዋሚዎች ግዜ ኣነሰብን ኢህኣዴግ ከእኛ በላይ ለምን ግዜ ተሰጠው ብሎም በቀጥታም በተዘዋዋሪ መንገዶች ሲኮንኑ ታይተዋል። ያ የግዜ ስሌት እንዴት ሊሆን ቻለ? ሳይገባቸው ስለቀረ ኣይደሉም እንደዛ ያሉት። ኢህኣዴግ እንደ መንግስት በፓርላማ ባለው የወምበር ብዛት ኣንፃር የግዜ ድልድል እንደተደረገ ያውቃሉ። ይህንን ግን ኣይቀበሉትም። ጥቂቶች በብዙሃን ስር መሆን እንደሚገባቸው ኣለመቀበል የፈጠረው ነገር ነው። ታድያ ይህንን ኣለመቀበል እንዴት ነው ዴሞክራሲያዊነታቸው የሚገልፀው? እንደ እኔ ውስጣቸው ከሚያጋልጡት ኣንዱ ነገር መሆኑን ኣውቆ ስለዚህ ጉዳይ ማንሳት ኣልነበራቸውም። ኣርቆ የማሰብ ዓቅም ስለሚያንሳቸው ግን ይህንን ብንል ምን ማለት ነው? ህዝብን ማሳመን ይችላል ወይ ብሎ ነገሮች በረቀቀ መንገድ መርምሮ ወደ ህዝብ መቅረብ ነበረባቸው። ህዝብ የሚጠቅም ነገር እንዴት እንፍጠር? ህዝብስ ከእኛ ምን ይጠብቃል ብሎ ትክክለኛው መልስ ማስቀመጥ ነበረባቸው። ያንን እንዳያደርጉ ግን ባህሪያቸው በጣም ነው የሚገድባቸው።

የሚቀጥለው ምርጫ ሰላማዊ ምርጫ እንዳይሆን ብዙ ውጣ ውረድ የሚሉ ሓይሎች በውስጥም በውጭም እንዳሉ የሚታወቅ ነው። እነዚህ ሓይሎች ኢህኣዴግ እንዳይመረጥ የሚፈልጉ ሓይሎች ናቸው። እንዲህ የሚሆኑት በቂ ምክንያት ኣላቸው። ምክንያታቸው ድብቅ ኣይደለም። ኢህኣዴግ ቢመረጥ የስልጣን ዕድሜውን ቢቀጥል እነሱ የፈለጉትን ነገር ማሳካት ኣይችሉም። እንደፈለጉት ኢትዮጵያን ማዘዝ ኢትዮጵያን መጠቀም ኣይችሉም። ባለፉት 18 ዓመታት በሚገባ ይህንን ነገር ኣይተውታል። በኢህኣዴግ መንግስት ሁሉም ነገር ከሽፎባቸዋል። ኢህኣዴግ በስልጣን በቆየበት ፍላጎታቸው የማሳካቱን በሮች በይበልጥ እየተዘጉ እንደሚሔዱ በሚገባ ተገንዝበውታል። የኢህኣዴግ መመረጥ በይበልጥ ውጥረት ውስጥ እየገቡ እንደሚሔዱ ያለፉት 18 ዓመታት ኣሳይተው ኣልፈዋል። ኢትዮጵያ ከደህነት ብትወጣ ደግሞ ጉዳያቸው ኣከተመ ማለት መሆኑን በሚገባ ያውቃሉ። ኢትዮጵያ ከደህነት የምትወጣው በኢህኣዴግ መንግስት ብቻ መሆኑንም ኣምነዋል። ስለዚህ ዓላማቸውና ፍላጎታቸውን ኢህኣዴግ በስልጣን እያለ እንኳን በኢትዮጵያ

ውስጥ በአፍሪካም ጭምር በሮች እየተዘጉባቸው እንደሚመጡ አይተውታል። ስለዚህ ኢህአዴግ እንዳይመረጥ ምርጫው ሰላማዊ እንዳይሆን የተቻላቸውን ያህል መድከም ነገሮችን ማበላሸት ፍላጎታቸውን ለማሳካት ተላላኪዎች ማደራጀትና መቅጠር ይኖርባቸዋል።

ምርጫውን ለማወክ የሚፈልጉት ሓይሎች ስራውን በቀጥታ በእነሱ በኩል አይፈፅሙትም። እሳት ጎርሶ የሚጠብቃቸው እንዳለ ከማናኛውም በላይ ያውቃሉና። ስለዚህ በተላላኪ በኩል ነው ያ ነገር ለማሳካት የሚፈልጉት። እሳት ውስጥ ገብቶ መቃጠል አይደፍሩትምና።

ኢህአዴግ ለምርጫው ሰላማዊነት የበኩሉን ዝግጅት ማድረጉን የሚታወቅ ነው። ይህ ማለት ምርጫውን ለማኮላሸት ለሚደረገውን እንቅስቃሴ በሙሉ አስፈላጊ ነው የተባለውን መፍትሔ እንደሚወስድ ከአሁኑ ማወቅ ይቻላል። በዚህ ምርጫን የመረበሽ ጉዳይ በግልም በመደራጀትም ለሚፈፀመው ስራ ተገቢውን ቅጣት መስጠት ተገቢ ይመስለኛል። ይን የአገር ጉዳይ ነው። የህዝቡን መብት አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውም እንቅስቃሴ እንዲቆም የማድረግ ሓላፊነት መንግስት እንዳለው ተገንዝቦ እጅና እግርን መሰብሰብ ያስፈልጋል። አንድ ሰው ወይም ድርጅት መብቱ የሚጠበቅ የብዙሃኑ ወይም የህዝቡን መብት ሲጠብቅ ብቻ ነው። አንድም ግለ ሰብ የመምረጥ መብቱን የሚገፍፍ አካል ቢመጣ መንግስት የግለ ሰቡን የመምረጥ መብት እንዳይገፈፍ በመብት ገፋፊው ግለ ሰብም ሆነ ድርጅት እርምጃ የመውሰድ ሓላፊነት ይኖርበታል። መንግስት ምርጫው ለማደናቀፍ ማንኛውም እንቅስቃሴ ቢፈጠር ያንን የተፈጠረውን ነገር ለመቆጣጠር የሚወስደውን እርምጃ ትክክል ነው ብቻ ሳይሆን ለዴሞራሲ ከመቆም የሚመጣ ትክክለኛው መፍትሔ ነው። ከሕግ በላይ ለሚሆነው ሁሉ ግለሰብም ሆነ የተደራጀ ሓይል ሕግ የበላይነት ያለበት መሆኑን በሚገባው ቋንቋ እንዲገባው ማድረግ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም ይሆናል። ጥቂቶች እንዳይጎዱ ተብሎ ሕግና ህዝብ የሚጎዳበት ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖርም። ምን ግዜም ሕግ የበላይነት እንዲኖረው መንግስት ሓላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል።

ሕግ መከበር ያለበት በሁሉም ዘንድ ቢሆንም መንግስት ግን በሕግ አስከባሪነት ታላቁን ስፍራ ይኖርበታል። ምርጫውን ሰላማዊ ለማድረግ በየግዜው የሚፈጠሩት አዋጆችና ሕጎች የማክበርና የመቀበል የሁሉም ዜጋ ግዴታ ነው። ይህንን ግዴታ ከግለ ሰብ እስከ የተደራጀ ሓይል ግዴታ ይሆናል። ስለዚህ ሁሉም በምርጫው ግዜ በምርጫው ስፍራ የሚገኙ በሙሉ ሰላማዊ እንዲሆንላቸው ዘንድ ሓላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል።

በምርጫው ሰላማዊነት ዋነኛ ተጠቃሚ ህዝቡ ነው። ስለሆነ ደግሞ ምርጫው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆን ዘንድ ህዝብ የበኩሉን ማድረግ ያለበት ይመስለኛል። በዚህ ጉዳይ ወጣቶች ከማንኛውም የሕብረተሰቡ ክፍል በላይ ምርጫው ሰላማዊ እንዲሆን ጠንክረው መስራት ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም የሃገሪቱን ተቀባዮች ናቸውና። ኢትዮጵያ ተቀብለው የማስቆየትና ለሚቀጥለው ትውል የማስተላለፍ ግዴታና ሓላፊነት አለባቸውና። የበለፀገችና ሰላምዋን የተጠበቀች አገር በማድረግ ረገድ ሓላፊነታቸውን በመወጣት ኢትዮጵያን የመጠበቅ ግዴታቸውን ከማንኛው

ግዜ የሚያረጋግጡበት ወቅት በዚህ ምርጫ ይመስለኛል። የዚህን ምርጫ ሓላፊነታቸው ባይወጡ የምርጫው አለማሳካት ወይም መበጣበጥ የመጀመርያ ሰለባ የሚሆኑት ወጣቶቹ ናቸው። ይህንን ቢከሰት ደግሞ በሚቀጥለው ትውልድ ተወቃሽና ባልተረጋጋች ኣገር ተበዳዮቹ ወጣቶቹ ይሆናሉ።

ከ60ዎቹ ወዲህ ወጣቶች ስለ ኣገራቸው የከፈሉት መስዋእትና ያካሔዱት ትግል ኢትዮጵያ እንደ ኣገር እንድትቆይና ትክክለኛው የዕድገት መንገድ እንድትከተል ኣድርገዋል። የዛን ግዜ ወጣቶች ለሂወታቸው ሳይሳሱ ሂወታቸውን መስዋእት ኣድርገው ያለፉት ለኢትዮጵያ መልካምና ዕድገት የከፈሉት ዋጋ ነበር ለትግል የበቁት። በዛን ግዜ ከወጣቶቹ የተጠበቀው ሂወታቸው መክፈል ነበር። ወጣቶቹ ኣገራቸውና ህዝባቸው የጠየቃቸውን ኩሉም ዓይነት መስዋእት ከልብ ኣምነው መልሰዋል። ጥያቀው ለመመለስ ከባድ ዋጋ ተከፍሎበታል። በኣሁኑ ወቅት ያንን ያህል ከባድ ነገር ኣይጠበቅም ከኣሁኑ ወጣቶች። ኣሁን ከወጣቶቹ የሚጠበቀውን ነገር መመለስ ባይችሉ ግን ከ60ዎቹ ጥያቄ በጣም የከበደ መልስ የሚያስፈልገው ሁኔታዎች መምጣታቸው የማይቀር ነው። ስለዚህ ወጣቶቹ የወደፊት ዕድላቸው መንገድ ማስያዝ የሚኖርባቸው ኣሁኑ ነው። ይህ ኣሁን መስራት ያለባቸው ጉዳይ ለወደፊቱ ዕድላቸው ወሳኝ ሚና ያለበት ነው የሚሆነው። ለዚህም ነው ወላጆቻችን ቀድሞ ለመዘጋጀት ታምሞ ከመማቐቅ ኣስቀድሞ መጠንቀቅ ያሉት። ትክክለኛ ኣባባል ነው። ወላጆቻችን ግን በተሟላ መልኩ በተግባር ኣላሳዩንም። ኢትዮጵያ በተሟላ መንገድ ኣላስረከቡንም። ለዚህም ነበር የ60ዎቹ ወጣቶች ለትግል የበቁት። እኛም ብንሆን የ60ዎቹ ወጣቶች ተከትለን ለትግል በቃን ታገልን። ያ ዓይነቱ ትግል ኣሁን ኣክትመዋል። የኣሁኑ ወጣቶች ደግሞ በሰላማዊ መንገድ የተረጋጋች ኢትዮጵያ የማድረግ ሓላፊነታቸው ከማንኛው የሕብረተሰቡ ክፍል በላይ መጫወት ይኖርባቸዋል። እኛ ያሳለፍነው የጦርነት ሂወት በወጣቶቹ ዘንድ መደገም እንዳይመጣ የማድረግ ዓቅም ያላቸው ወጣቶቹ የሕብረተሰቡ ክፍል ናቸው።

ረብሻ ሁከት ለማንም ኣይበጅም። ይህ በሂወት ዘመናችን ያየነው ሓቅ ነው። በተለይ በተለይ ግን ለወጣቱ ክፍል ኣይበጅም። ኣንድ ኣገር ሰላምዋን የሚጠበቅ የሕግ የበላይነት ሲረጋገጥ ብቻ ነው። ይህንን የማረጋገጥ ወሳኙ ሚና የሚጫወተው ደግሞ ወጣቱ ክፍል ነው። መጪውን ምርጫ እንዲከላሽ ፈላጊ ሓይሎች ስራውን ማስፈፀም የሚፈልጉት በወጣቱ ክፍል በኩል ነው። ለምን ዓቅሙ ያለው በወጣቱ ላይ ስለሆነ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ወጣት የእነዛን ሓይሎች መጠቀምያ መሆን የለበትም። መንግስት ሕግን የማስከበር ግዴታና ሓላፊንቱን መወጣት ይኖርበታል የተረጋጋች ኣገር ለማረጋገጥ። ወጣቱ ትውልድ ከመንግስት ጋር በመሆን ኢትዮጵያን መጠበቅ ይኖርበታል። የኣገሪቱን ወራሽ ነውና። ገና ከኣሁኑ ለችግር ለደህነት ለሁከትና ለስደት እንዳይዳረግ ኢትዮጵያን ከማንኛው ዓይነት ጉዳት መከላከልና መጠበቅ ኣለበት። ታምሞ ከመማቀቅ ኣስቀድሞ መጠንቀቅ ብቸኛው የመጪውን ዕድሉ የመወሰኛ ዘዴና ትክክለኛው ብልሓት ነው። ምርጫውን የመበላሸት ኣጋጣሚ ይመጣል ከሚል ስጋት የለኝም። ኢህ ኣዴግ እስካለ ድረስ በጣም ከልብ መተማመን ይቻላል። ወጣቱ እንዳይሳሳት ወጣቱ ኣደጋ ውስጥ እንዳይገባ ከማለት ነው ከረብሻ የሚመጣውን ጉዳት ለማሳየት የመኮርኩት።

በምርጫው ተወዳዳሪ ድርጅቶችም ቢሆኑ የፌታችን ምርጫ ሰላማዊ የማድረግ ግዴታቸው መዘንጋት አይገባቸውም። እንደ 97ቱ ሁከት ማንሳት በሁከተኞች ላይ የሚመጣውን ጉዳት ከአሁኑ መገመት ተገቢ ነው። በምርጫው ውጤት ደስተኞች ባይሆኑ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ጉዳያቸው ማየት እንጂ ብጥብጥ ማንሳትና መጫር ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለእነሱ የሚበጀው ፋይዳ አይኖርም። በኢትዮጵያ ውስጥ ያንን ዓይነት ነገር ፋሺኑ አልፎበታል። በአሁኑ ኢትዮጵያ ሁሉም ነገር በሕጋዊ መንገድ መፍትሔ ማበጀት በተቻለበት ግዜ ሁከትና ረብሻ ከመጠን በላይ ጉዳት ብቻ ነው ውጤቱ። ኢትዮጵያ ለሁሉም ዓይነት ሰላማዊ ትግል ማስተናገድ ትችላለች። ከሰላማዊ መንገድ ባሻገር ማስተናገድ ግን በኢትዮጵያ ምድር ከንቱ ድካም ብቻ ነው የሚሆነው። በ97ቱ ምርጫ ለተከሰተው ረብሻ አስተባባሪዎችና ፈፃሚና አስፈፃሚዎች መንግስት በይቅርታ አይቶ ተገቢ መፍትሔ ሰጥቶበታል። ያንን ዓይነት መፍትሔ ግን ከአሁን በኋላ በበኩሌ የሚደገም አይመስለኝም። መደገሙንም በኢትዮጵያ ህዝብ በደል መፈፀም ይመስለኛል። ከመንግስት ያንን ዓይነት ነገር እንደማይደገም የሚያሳዩ ነገሮች ስንከታተል ቆተናል። ያከተመበት ነገር ነው ማለት ነው። ስለዚህ ተቃዋሚ ድርጅቶች ከእነዛ የ97ቱ ዓይነት አስቀያሚ ስራ መቆጠብ ይጠብቃቸዋል። ያንን ባያደርጉ የሚገጥማቸውን ከአሁኑ መገንዘብ ሳያስፈልጋቸው አይቀርም። ታምሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ተገቢና ተወዳዳሪ የማይገኝለት የወደፊቱ መፍትሔ ይመስለኛል።

በውጭ በተለያየ የዓለማችን ክፍል የምንገኘው ኢትዮጵያውያን ሰላማዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ኣገራችን እንዲደረግም ሓላፊነታችን መወጣት ይኖርብናል። በተለያዩ ኣጋጣሚዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ሁከት እንዲኖር የሚያስችሉ ብዙ ነገሮች ከኢትዮጵያው ውጭ በሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ሲሰሩ ቆይተዋል። ኣሁንም ይህንን ምርጫ ሰላማዊ እንዳይሆን የተቻላቸውን ያህል እያደረጉ ይገኛሉ። በተለይ ግዜና መድረክ የከዳቸው የደርግ የኢህኣፓ የመኢሶን ታጋዮች የነበሩ ሰዎች እንደ ኣዲስ በሌላ ስም ተጠምቀው ሽርጉድ ውስጥ ከገቡ በጣም ቆይተዋል።

ብዙ ሙሁራን ኢትዮጵያውያን በተማሩት ኣገራቸውን መጥቀም ሲገባቸው ኣገራቸውን እየጎዱ ይገኛሉ። ይህንን ዓይነት አስነዋሪ ስራ ማቆም ያለባቸው ይመስለኛል። ስልጣን የማግኘት ፍላጎታቸውን ከንቱ ድካም መሆኑን ቀድሞ ማየት መቻል ነበረባቸው። ኢትዮጵያን ማገዝ ኢትዮጵያን ማሳደግ በሚችሉበት መንገድ ቢመጡ ኢትዮጵያ እጅዋን ዘርግታ ትቀበላቸዋለች። ኢትዮጵያ ከምሁራኑ የምትፈልገው ያንን ብቻ ነው። በሌላ መልኩ ግን ፈቃደኛ ኣለመሆንዋን ከኣሁኑ ማወቅ ይገባቸዋል። የሰው ልጅ ዕድሜ ልኩ እየተሳሳተ አይኖርም ጤነኛ አእምሮ ካለው። የእኛ ምሁራን ግን በስሕተት ውስጥ እንደተዘፈቁ መውጣት አቅታቸው ለብዙ ዓመታት እዛው ውስጥ ይኖራሉ። ከኣሁን በኋላ የመውጣታቸው ጉዳይም ኣጠራጣሪ ነው። ዕድላቸው ነውና በዛን በማይሆነው ነገር ተስፋን ሰንቀው እስከ ዘመነ ሂወታቸው መጨረሻ መቆየት ብቻ ነው ዕጣቸው። ይህ በእውነት መረገም ነው።

ሌላውን ያልተማረ ህዝብ የሙሁራኑ ተከታይ ሙሁራኑ የሚሰብኩት ነገር ይፈፀማል በማለት ሙሁራኑ ለጠየቁት ገንዘብ ለራሱ ሳይጠግብ ኑሮውን ሳያሻሽል የቻለውን ብቻ ሳይሆን ሙሁራኑ የጠየቁት ይሰጣል። በማያውቀው ነገር እነሱን ተከትሎ

በማይጨበጠው ሓሳብ ይበራል። የት ነው ማረፍያህ ብትለው ግን በምንም ተኣምር ኣያውቀውም። ቤተሰቦችህን እንዲጨፈጨፉ ገንዘብ ኣዋጣ ሲሉት መስጠት ብቻ ነው የሚያውቀው። ምሁራኑ ሰርተው ማግኘት የማይችሉት ገንዘብ በሚስኪኑ ህዝብ ገንዘብ ይንደላቀቃሉ። ይህ ህዝብ ከኣንቀላፋበት ነቅቶ ነገሮችን መመርመር ያስፈልገዋል። ከጠላቶቹ ጋራ ኣብሮ መኖሩ ቆይቶ እንደሚጎዳው ከኣሁኑ ማወቅ ይኖርበታል። ኋላ ከእንቅልፉ ሲባንን ግዜ ወይ እኔ እነዚህ ደደቦች ተጫወቱብኝ ኣታለሉኝ ከማለት ገና ከኣሁኑ ታምሞ ከመማቀቅ ኣስቀድሞ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በውጭ የምንገኘው ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያን ከሚጎዳ ህዝባችን ስቃይ ውስጥ ከሚዳርግ ነገር መቆጠብ ይኖርብናል። ኢትዮጵያ ከየትም የዓለማችን ኣቅጣጫ እንጠብቃት። ኣንካዳት እናታችን ናትና። ኢትዮጵያውነታችን በትውልዳችን ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር ማረጋገጥ ያለብን ይመስለኛል።

ከምርጫ በፊት በሌላ ኣጋጣሚ ካልተገናኘን ሰላማዊና የተረጋጋ ምርጫ እንዲሆንልን ከልብ እመኛለሁ።

ሃይለ (ተጋዳላይ) gedliweyn@yahoo.com

ከኣውስትራልያ